Time: Kronos and Kairos

ጊዜ፡ ክሮኖስ እና ካይሮስ

የጊዜ ዋጋ

- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ እኩል የሰጠው ስጦታ ጊዜ ነው።
- የተለያየ ቁመት፣ የተለያየ አስተዳደግ፣ የተለያየ የቆዳ ቀለም፣ የተለያየ ቤተሰብ፣ የተለያየ ባህል ... አለን።
- ሁላችንም ግን አንድ አይነት ያለን ነገር ጊዜ ነው።
- ለማኝም፣ ቢሊየነርም አንድ አይነት ያላቸው ነገር ጊዜ ነው። ሁለቱም በደቂቃ ውስጥ 60 ሰከንድ፣ በሰዓት ውስጥ 60 ደቂቃ፣ በቀን ውስጥ 24 ሰዓት ... አላቸው።

- ጊዜን ልናቆመው ባንችልም፥ ልንቆጣጠረው እና ለጥቅማችን ልንጠቀመው እንችላለን።
- Time is unstoppable but controllable
- A new season is an opportunity
    - to refine your purpose, to go back and check it
    - To redefine your life vision,
    - Bury the past and move into a new future

- የምትሆኑት ነገር በጊዜያችሁ በምታደርጉት ላይ የተመሰረተ ነው
- What you do with time determines who you become

በግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ለሚለው ቃል ሁለት ቃላት አሉ፡ ክሮኖስ (Kronos) እና ካይሮስ (Kairos)

ክሮኖስ (Kronos)

- መለካት የሚችለው ጊዜ
- የጊዜ ርዝመት
- በተለምዶ ጊዜ ወይም ሰዓት ብለን የምንጠራው።
- በሰከንድ፣ በደቂቃ፣ በሰዓት፣ በቀን እና በአመት የሚመዘነው ጊዜ
- ሁልጊዜም ያለ ጊዜ፣ ያልተገደበ ጊዜ
- ለሁሉም ሰው እኩል እና አንድ አይነት ነው
- The quantity of time

ካይሮስ (Kairos)

- የተወሰነው ጊዜ
- ትክክለኛው ጊዜ
- የእድል ጊዜ/ Time of opportunity
- ሁልጊዜም የሚገኝ አይደለም፣ የተገደበ ጊዜ
- ትንቢታዊ / መለኮታዊ የሆነ ጊዜ ነው
- The quality of time

Kairos is Person-specific

የአንዱ ካይሮስ ለሌላው ክሮኖስ ሊሆን ይችላል።

<u>ለሁሉም ነገር ካይሮስ አለው</u>

“ለሁሉም ነገር ጊዜ (ካይሮስ) አለው፤ ከሰማይ በታች ለሚከናወነው ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው፤” መክብብ 3፡1-8

“እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “በቀላሉ እንዲነቡ፣ ራእዩን ጻፈው፤በሰሌዳም ላይ ቅረጸው። ***<u>ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና</u>***፤ ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤እርሱም አይዋሽም፤የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤በርግጥ ይመጣልና፤ ከቶም አይዘገይም።” ዕንባቆም 2፡2

ራዕዩ (እግዚአብሔር ሊያደርግ ያቀደው) የተወሰነለት ካይሮስ ጊዜ አለው። ይህንን ጊዜ ሳንረዳ ስንቀር የዘገየ ቢመስለንም ነገር ግን በጊዜው ይሆናል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመመላለስ መለኮታዊ ጊዜን መረዳት አለብን።

<u>ካይሮስን ዋጁ/አታባክኑ</u>

“እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ። ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን (ካይሮስን) በሚገባ ዋጁ። ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ። 18በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና።” ኤፌሶን 5፡1-18

ካይሮስ ጊዜን ዋጁ ማለት የተወሰነው ጊዜ እናዳያመልጣችሁ አድኑ ማለት ነው።

ካይሮስ ጊዜ በባህሪው የሚያልፍ ጊዜ ነው። ሁልጊዜ የሚገኝ ጊዜ አይደለም። ስለዚህ ሰዎች ሳያውቁት ወይም ሳይረዱት እግዚአብሔር የወሰነውን ልዩ ጊዜ (ካይሮስ) እንደ ሌላ ተራ ጊዜ (ክሮኖስ) ቆጥረው ሊያልፉ ይችላሉ። ስለዚህ ጊዜውን መዋጀት ማለት እግዚአብሔር

የወሰነውን እና የሚሰራበትን ጊዜ መረዳት እና በሚገባ መጠቀም ነው።

<u>በክሮኖስ የምታደርጉት በካይሮስ የሚሆነውን ይወስናል።</u>

What you do with your kronos will determine what happens with kairos
እግዚአብሔር የቀጠረው ትንቢታዊው ጊዜ (ካይሮስ) እስኪመጣ ድረስ በእያንዳንዱ ጊዜ የምናደርገው ነገር በጣም ወሳኝ ነው።

ማቴዎስ 25፡1-13 ላይ ያሉት አስሩ ደናግል አንድ አይነት ሁኔታ ላይ ነበሩ። ተመሳሳይ ጊዜ እና ተመሳሳይ እድል ደረሳቸው። የእነርሱ ካይሮስ የሙሽራው መምጣት ነበር። ነገር ግን ሁሉ እኩል አልተጠቀሙትም ነበር። አምስቱ ደናግን ካይሮሱ ጊዜ እስኪመጣ በክሮኖስ ጊዜያቸው ውጤታማ እና ዘይትን ይዘው ተዘጋጅተው የሚጠብቁ ነበሩ። በክሮኖስ የምታደርጉት በካይሮስ የሚሆነውን ይወስናል።

“ሌላም ነገር ከፀሓይ በታች አየሁ፦ ሩጫ ለፈጣኖች፣ ውጊያም ለኀያላን አይደለም፤ እንጀራ ለጥበበኞች፣ ወይም ባለጠግነት ለብልሆች፣ ወይም ሞገስ ለዐዋቂዎች አይሆንም፤ ጊዜ (ክሮኖስ) እና ዕድል (ካይሮስ) ግን ሁሉን ይገናኛቸዋል።” መክብብ 9፡11

በሰዎች መካከል ልዩነትን የሚያመጣው የጊዜያቸው አጠቃቀም እና የሚደርሳቸውን መለኮታዊ እድል በውጤታማነት መጠቀማቸው ነው።

ዘመናትን መመርመር

እግዚአብሔር ሰዎች ጊዜን እንዲለዩ (discern) ይፈልጋል።
በመንፈሳዊው አለም ጊዜ በጣም አስፈላጊዜ ነው።

“የጠቢብም ልብ ጊዜንና ፍርድን ያውቃል።” መክብብ 8፡5
“ጥበበኛም ልብ ትክክለኛውን ጊዜና ተገቢውን አሠራር ያውቃል።” መክብብ 8፡5 (አ.መ.ት.)
"a wise man's heart discerns both time and judgment" (Eccl. 8:5).

“ደግሞም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ “ደመና በምዕራብ በኩል ሲወጣ ስታዩ ወዲያው፣ ዝናብ ሊመጣ ነው ትላላችሁ፤ እንደዚያም ይሆናል፤ የደቡብ ነፋስም ከደቡብ በኩል ሲነፍስ፣ ቀኑ ሞቃት ይሆናል ትላላችሁ፤ እንደዚያም ይሆናል። እናንት ግብዞች፤ የምድሩንና የሰማዩን መልክ መመርመር ታውቁበታላችሁ፤ ***ታዲያ ይህን የአሁኑን ዘመን መመርመር እንዴት ተሳናችሁ?***” ሉቃስ 12፡54-56

ኢየሱስን ሽቱ የቀባችው ሴት

ማቴዎስ 26፡6-13

6 ኢየሱስም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ፥
7 አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች በማዕድም ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
8 ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተቈጡና። ይህ ጥፋት ለምንድር ነው?
9 ይህ በብዙ ዋጋ ተሸጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና አሉ።

10 ኢየሱስም ይህን አውቆ እንዲህ አላቸው። መልካም ሥራ
ሠርታልኛለችና ሴቲቱንስ ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ?
11 ***<u>ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ
ጋር አልኖርምና፤</u>***
12 እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች።
13 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም
ስፍራ በሚሰበክበት እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ
እንዲሆን ይነገራል።

ይህች ሴት ኢየሱስ ለአጭር ጊዜ በመካከላቸው እንዳለ ተረድታ ነበር። ሌሎቹ ግን እርሱ ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር የሚኖር መስላቸው ነበር (ጊዜው ካይሮስ እንጂ ክሮንኖስ እንዳልሆነ አልገባቸውም)። ለዚህ ነበር ኢየሱስ እርሱ ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደማይኖር የነገራቸው።

ሌሎች ሴቶች ነበሩ ሽታቸውን የቀጠቡ። ምናልባትም እነርሱም እንደሌሎቹ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ስለሚኖር ሌላ ጊዜ እንቀባዋለን ብለው አስበው ሊሆን ይችላል። **ሌሎቹ ሴቶች ግን የካይሮስ መረዳት አልነበራቸውም። ነገር ግን እንዳሰቡት ሳይሆን ሞተ። በዚያን ጊዜ ሬሳውን ሊቀቡ መጡ ነገር ግን ሰንበት ሊገባ ስለነበር መቀባት አልቻሉም፤ ከሰንበት በኋላም ሊቀቡት ሲሄዱ ተነስቶ ነበር** (ማርቆስ 16፡1-7)። ሽታቸውን ሳይቀቡት አለፈባቸው። ኢየሱስ ይህንን በትንቢት መንፈስ ስለተመለከተ ነበር “እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች።”

<u>የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የካይሮስ መረዳት አልነበራቸውም</u>

ማርቆስ 14

32 ጌቴሴማኒ ወደምትባልም ስፍራ መጡ፥ ደቀ መዛሙርቱንም። ስጸልይ ሳለሁ፥ በዚህ ተቀመጡ አላቸው።
33 ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረና።
34 ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቈዩ ትጉም አላቸው።
35 ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በምድርም ወድቆ፥ ይቻልስ ቢሆን ሰዓቲቱ ከእርሱ እንድታልፍ ጸለየና።
36 አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ።
37 መጣም ተኝተውም አገኛቸው፥ ጴጥሮስንም። ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን? አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጋ አልቻልህምን?
38 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።
39 ደግሞም ሄዶ ያንኑ ቃል ጸለየ።
40 ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው፥ የሚመልሱለትንም አላወቁም።
41 ሦስተኛም መጥቶ። **እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ ይበቃል፤ ሰዓቲቱ ደረሰች፤** እነሆ፥ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።
42 ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።

ደቀመዛሙርቱ መጸለይ እንደሚገባቸው ቢረዱም ነገር ግን ከጊዜ ጋር ሩጫ ላይ እንዳሉ አልተረዱም ነበር። የችኩልነት ስሜት (a sense of urgency) አልነበራቸውም።

የመጸለይ ጊዜ ስለነበር ኢየሱስ ሁለት ጊዜ 'ትጉ' እና 'ወደፊተና እንዳትገቡ ጸልዩ' አላቸው። እነርሱ ግን አስቸኳይ የሆነ የጸሎት ጊዜ እንደሆነ ስላልተረዱ ተኙ። ምናልባትም 'ጸሎት የት ይሄድብናል' ብለው አስበው ሊሆን ይችላል። በሶስተኛው ጊዜ ግን ኢየሱስ ጸልዩ ሳይሆን ያላቸው '***<u>ተኙ ዕረፉም</u>*** ነበር። ለምን? ምክንያቱም ጊዜው ስላለፈ። ለዚህም ነበር '***<u>ሰዓቲቱ ደረሰች</u>*** ያለው። Jesus was time conscious but the disciples were not!

<u>ኢየሩሳሌም ካይሮስን አልተረዳችም</u>

ሉቃስ 19

41ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሲቃረብ ከተማዋን አይቶ
አለቀሰላት፤ 42እንዲህም አለ፤ "ሰላምሽ የሚሆነውን ምነው
አንቺ ዛሬ በተረዳሽ ኖሮ! አሁን ግን ከዐይንሽ ተሰውሮአል፤
43ጠላቶችሽ ዙሪያሽን ቅጥር ሠርተው፣ ከየአቅጣጫውም
ከበው አንቺን የሚያስጨንቁበት ጊዜ ይመጣልና፤ 44አንቺንና
በቅጥርሽ ውስጥ የሚኖሩትንም ልጆችሽን ከዐፈር
ይደባልቃሉ፤ ድንጋይም በድንጋይ ላይ አይተዉም፤
የመገኰበኛሽን ጊዜ አላወቅሽምና።"

የእግዚአብሔር ከተማ ኢየሩሳሌም የመጎብኛዋን ጊዜ፥ እግዚአብሔር የወሰነውን ጊዜ፥ ትክክለኛውን ጊዜ፥ ካይሮሱን ጊዜ ባለማወቋ ወደከፋ ሁኔታ ውስጥ እንደምትገባ እንመለከታለን። ኢየሩሳሌም የተለየ መለኮታዊ ጊዜ ላይ እንደሆነች አልተረዳችም ነበር።

ጊዜውን ጠብቁ

“ባንዝልም ***በጊዜው*** እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።” ገላትያ 6፡9
“እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ” 1ኛ ጴጥሮስ 5፡6

እግዚአብሔር ማሽን ሳይሆን ስብዕና ያለው አምላክ ስለሆነ እኛ አይደለንም ጊዜውን የምንወስንለት። እርሱ የራሱ የሆነ ጊዜ አለው። እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ጊዜ ስላለው መዛል የለብንም። ነገሮች እኛ ባሰብናቸው ፍጥነት እና ጊዜ ባይሆኑም እንኳ መልካምን ነገር ለማድረግ መታከት የለብንም።

የማጨድ ጊዜ አለ፣ የመጎብኘት ጊዜ አለ፣ የትንቢት መፈጸም ጊዜ አለ፣ የከፍታ ጊዜ አለ።

መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ደመናት ዝናብን በሞሉ ጊዜ በምድር ላይ እንደሚያፈሱ” ይናገራል። ስለዚህ የምናደርገው መልካም ነገር ሁሉ ደመናችንን እየሞላ ነው። ትንቢታዊው ጊዜ በደረሰም ጊዜ ዝናቡ ይመጣል።

በእንግሊዘኛ እንዲህ የሚል መዝሙር አለ፡

Don't be tired in work
Don't be tired in faith
Don't be tired in praying
Cause we don’t know when He will come

በስራችሁ አትድከሙ

በእምነታችሁ እትድከሙ
በጸሎታችሁ እትድከሙ
ምክንያቱም መቼ እንደሚመጣ አናውቅምና

ዳንኤል 2

20፤ ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ። ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና
የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤
21፤ **<u>ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል</u>**፤ ነገሥታትን ያፈልሳል፥
ነገሥታትንም ያስነሣል፤ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም
ለአስተዋዮች ይሰጣል።
22፤ የጠለቀውንና የተሠወረውን ይገልጣል፤ በጨለማ ያለውን
ያውቃል፥ ብርሃንም ከእርሱ ጋር ነው።
23፤ ጥበብንና ኃይልን የሰጠኸኝ፥ እኛም የለመንንህን ነገር አሁን
ያስታወቅኸኝ፥ አንተ የአባቶቼ አምላክ ሆይ፥ የንጉሡን ነገር
አስታውቀኸኛልና እገዛልሃለሁ አመሰግንህማለሁ።

In Jesus’ name God is changing times and seasons in your life!
በኢየሱስ ስም እግዚአብሔር በህይወታችሁ ጊዜያትን እና ዘመናትን እየለወጠ ነው!